የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

የሰበር መ/ቁ 250459

ሰኔ 28 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች: ብርሃኑ አመነው

በእውቀቱ በላይ

ቀንዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- 1.ወ/ሮ አብጊያ አብደታ ያደሳ - ቀረቡ

2. አቶ ብርሃኑ ሰይፉ ዲነግዴ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሰናይት ታደሰ አለሙ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ በፍትሃብሄር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 6 መሰረት ዳግም ዳኝነት እንዲታይ የቀረበ አቤቱታን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/174750 በቀን 29/10/2015 ዓ.ም የተሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ይታረምልኝ ሲሉ አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ባቀረበችው ክስ አመልካቾች ድንበር ገፍተዉ የተጠሪ ይዞታ ላይ የፈጸሩት ሁከት እንዲወገድ የሚል

ሲሆን በፍርድ ቤቱ ማስረጃ መስቶና መርምሮ አመልካቾች ድንበር ገፍተዉ በተተሪ ይዞታ ላይ የፈጸሩት ሁከት እንዲወገድ በማለት በመ/ቁ/174750 ላይ በቀን 21/04/2014ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በዳግም ዳኝነት ሊታይልን ይገባል ሲሉ አመልካቾች በቀን 17/6/2015 ዓ.ም አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን በዚህም ለፍርድ ቤቱ ውሳኔ መነሻ የሆነው የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በባለሙያ በ06/4/2014 ዓ.ም የሰጠው ምላሽ በሀሰተኛ የምስክር ቃል በሀሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሰነድ እንደሆነ ከወረዳ መሬት አስተዳደር እስከ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ፅ/ቤት ድረስ ቅሬታ አቅርበን በተደረገው ማጣራት ምላሹ ሀሰተኛ መሆኑ ተደርሶበት በመሀንዲስ ሪፖርት መሻሩን በቁጥር ለሚ ኩራ ክ/ከ/አስ/መ/ል/አስ/ፅ/ቤት/ 1266412/2015ዓ.ም በቀን 13/06/2015 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ አረጋግጠናል፤እውነታውም ባለሙያው ለፍ/ቤቱ በ06/04/2014ዓ.ም እንደፃፈው ሳይሆን ተጠሪ የአመልካቾችን ይዞታ ጭምር አካታ ካርታ ያሰራች በመሆኑ ሲሆን አመልካቾች የያዝነው የተጠሪ ይዞታ የለም፤የክፍለ ከተማው መሀንዲስም ከቀጠና አመራሮች እንዲሁም ከወረዳው መሬት ልማት ፅ/ቤት ጋር ባደረገው ማጣራት የተጠሪ ካርታ በሚሰራበት ጊዜ የአመልካቾች ይዞታ በከፊል ተካትቶ እንደተሰራላቸው በእስኬች የተደገፈ የመሀንዲስ ሪፖርት ቀርቧል፤ከለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 መሬት ልማት ፅ/ቤት፤ ከቀጠና አመራሮች፤የ97 አየር ካርታ ኮሚቴ፤ ከአርሶ አደር የተወጣጣ ኮሚቴ ተደራጅቶ ቦታው ድረስ በመሄድ ሰነዶችን በመመልከት በተደረገው ማጣራት በ1997 አየር ላይ ይታይ የነበረው የአመልካቾች ግንባታ ካርታ ሳይሰጥ ለተጠሪ በ2013 ዓ.ም ካርታ መሰጠቱ ከህግ ውጭ መስተንግዶ ያገኙ መሆኑን ያሳያል፤ካርታውም 2ኛ አመልካች ግቢ ውስጥ 64 ካ.ሜ ፤1ኛ አመልካች ይዞታ ደግሞ 113 ካ.ሜ ገብቶ ያለአግባብ የተሰራላቸው በመሆኑ ሊመክን እንደሚገባው የባለሙያውንም በሀሰት የተሰናዳ ምላሽ ፍርድ ቤቱ ቢያውቀው ኖሮ ፍርዱን ሙሉ በሙሉ ያስለውጥ እንደነበር ጠቅሰው መዝገቡ በድጋሚ ታይቶ አመልካቾች በተጠሪ ላይ የፈጠሩት ሁከት የለም አንዲባል፤የተጠሪም ካርታ በተገቢው ይዞታዋ ላይ ብቻ እንዲሰራ ሲሉ አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

ተጠሪም አቤቱታው ደርሷት በ20/7/2015 ዓ.ም ባቀረበችው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የዳግም ዳኝነት ጥያቄው የቀረበው ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩ እልባት ከሰጠ በኃላ በመዘግየት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6(3) እና 244(2)(ሰ) መሰረት የዳግም ዳኝነት እና ውሳኔ ይነሳለኝ ጥያቄ በአንድ ወር ይርጋ ቀሪ ሊደረግ ይገባል በማለት የተቃወመች ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል አይገባም? ለሚለው ጭብጥ አመልካቾች አቤቱታ ያቀረቡት ምላሽ ከተሰጠ ከአራት ቀን በኃላ በቀን 17/6/2015 ዓ.ም በመሆኑ የአመልካቾች አቤቱታ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይገባም ሲል ብይን የሰጠ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በቀን 21/4/2014 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በድጋሚ ሊታይ ይገባል አይገባም ለሚለው ጭብጥ አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ ቀድሞ ለፍርድ ቤቱ የተሰጠው ምላሽ ተሽሯል

ያሉበት ምክንያት ያልተገለፀና ከዚህ በፊትም የተሰጠው ምላሽ ስህተት በምን አግባብ እንደተፈጠረ ሳይገለፅ እራሱ የሰጠውን ማስረጃ እራሱ ስህተት ነው ያለበትን ምክንያት ማስረጃው አያመለክትም፤በመሆኑም ማስረጃው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6 የማያሟላና በወንጀል ተግባር የተገኘና በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ያልተገለፀ በመሆኑ ፍርዱ በድጋሚ ሊታይ አይገባም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ለዚህ ሰበር አቤቱታም የቀረበዉ በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች በሀምሌ 6 ቀን 2015 ዓ.ም ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፤አመልካቾች ያቀረብናቸው ማስረጃዎች ቀድሞ ለፍ/ቤቱ የተሰጠው ምላሽ በሀሰተኛ ቃል የተሰጠ መሆኑን በበቂ ሁኔታ ከመጥቀሱም በላይ ሀሰተኛና ትክክለኛ ባለመሆኑ መሻሩን፤ማስረጃው የቀድሞውን ምላሽ ሀሰተኛነት አያሳይም ቢባል እንኳ የስር ፍ/ቤት ሀሰተኛ በሚል የተሻረበትን ምክንያት በተጨማሪ ማብራሪያ ወይም ማስረጃ አስቀርቦ ማጣራት እንጂ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ/6 አላግባብ በመተርጎም ማስረጃው አያመለክትም ወይም ማመልከት ነበረበት በማለት ብቻ መከልከሉ ፍትህ የማስፈን ዓላማን ይቃወማል፤የቀድሞ ምላሽ ሀሰተኛነት በአሁኑ ማስረጃ ላይ አልተገለፀም የሚለው ምክንያት ትክክል አይደለም እንጂ ነው ቢባል እንኳ ይህን ክርክር ተጠሪ በመልሳቸው ላይ አላነሱትም ፍርድ ቤቱም በራሱ አንስቶ ብይን መስጠቱ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ/182/2 እና በሰበር መ/ቁ/25026 በቅፅ6 የተሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም ይቃረናል፤አመልካቾች ጥያቄውን ስናቀርብ መነሻ ያደረግነው ሰነዶች ተጠሪ ካርታ ሲሰራላቸው ከ1ኛ አመልካች ይዞታ 113 ካ.ሜ ፤ከ2ኛ አመልካች ይዞታ ደግሞ 64 ካ.ሜ እንደተወሰደ በእስኬች እና ከ1997 ዓ.ም አየር ካርታ ጭምር በግልፅ የሚያሳዩና በ17/04/2014ዓ.ም የተሰጠው ምላሽ በስህተት በመሰጠቱ መሻሩን የሚያስረዱ ሆኖ ሳለ ይህን ሳይታይ የተሰጠው ውሳኔ የማስረጃ ምዘናን እና የሰበር መ/ቁ/89676 በቅፅ 17 የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ጉዳዩ በድጋሚ ዳኝነት ሊታይ አይገባም የሚለው የብይን ክፍል በመሻር በስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በድጋሚ ዳኝነት ታይቶ እንዲወሰንልን ሲሉ ጥያቄያቸውን አቅርበዋል፡፡

የሰበር ችሎት አቤቱታዉን ተመልክቶ የስር ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ የተሰጠው ማስረጃ የተሻረ መሆኑን ባረጋገጠበት ሁኔታ በዳግም ዳኝነት ጥያቄው ቀድሞ የተሰጠው ማስረጃ ሀሰተኛና በወንጀል ተግባር የተገኘ ለመሆኑ በአስተዳደር አካል አልተገለጠም በሚል ዉድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ሰበር ችሎቱ /መ/ቁ/91968 ከተሰጠው ገዢ ትርጉም አንፃር ተገቢነቱን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡

ተጠሪ በ18/04/2016ዓ.ም መልስ ያቀረበች ሲሆን በዚህም የአስተዳደር አካሉ ውሳኔ የሚሰጥበት ማስረጃ በሌላኛው ተከራካሪ ወገን ባለበት የአንዱን ወገን አቤቱታ ብቻ አይቶና ሰምቶ በፍ/ቤት የተሰጠን ውሳኔ ማሻሩ የፍርድ ቤት ስልጣን ልዕልናን የሚጋፋ ነው፤የሀሰት ቃልና በሀሰት የተዘጋጀ

ማስረጃ በሚል የገለፁት ምንም ምስክር ባልተሰማበት፤ለምን፤በምን ምክንያት፤በየትኛው ተከራካሪ ወገን ተደርጓል ብለው ባልጠየቁበት የቀረበ ነው፤ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6 ድንጋጌንም አያሟላም፤የአስተዳደር ፅ/ቤቱ ራሱ ለሰጠው ማስረጃ ገለልተኛና ነፃ የሆነ ይግባኝ ሰሚም፤የዳኝነት ሰጪ አካልም ራሱን አድርጎ ለሰጠው ምላሽ አንደኛው ተከራካሪ ወገን ሲጠይቀው ለፍርድ ቤት አረጋግጬ የሰጠሁት የተሳሳተ ማስረጃ ነው በሚል ያቀረቡት ቅሬታ ተገቢነት የሌለው ነው፤በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቱ ብይን ፀንቶ ይወሰንልኝ በማለት ምላሽ ሰጥቷል፡፡አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በጥር 2 ቀን 2016 ዓ.ም አቅርበዋል ፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፤በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ ጉዳዩ ዳግም ዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በመደረጉን በመቃወም የቀረበ ነዉ፡፡

የፍትሐ ብሔር ክርክር በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተደነገገዉ አግባብ ተመርቶ የመጨረሻ እልባት አግኝቶ መቋጨት አለበት፡፡ክርክሮች የመጨረሻ ዉሳኔ ካገኙ በኂላ በዚያዉ አስቀድሞ የመጨረሻ ዉሳኔ ባገኘ ሥረ ነገር እና ጭብጥ ላይ አስቀድሞ በተከራከሩ ወገኖች መካከል ተደጋጋሚ ክርክር የሚደረግ ከሆነ የተከራካሪ ወገኖችን እና የፍርድ ቤቶች ጊዜ፣የሰዉና የገንዘብ ሀብት (judicial economy) ያለአግባብ ይባክናል፤እርስ በእርስ የሚጣረሱ ዉሳኔዎች የሚሰጥበትንም አለአስፈላጊ አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡ ይህ እንዳይሆን የሥነ ሥርዓት ሕጉ የመጨረሻ ዉሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ ድጋሚ አዲስ ክስ እንዳይቀርብ የሚከለክል መርህ *(Priniciple of Res Judicata)* ደንግጓል፡፡በመሆኑም ክርክሮች የመጨረሻ ዉሳኔ ካገኙ በኂላ በመርህ ደረጃ በድጋሚ እንዲታዩ የሥነ ሥርዓት ሕጉ አይፈቀድም፡፡ አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ዉሳኔ ካገኘ በኂላ በልዩ ሁኔታና በዉስን ምክንያት ዳግመኛ ዳኝነት የሚታይበትን ሥነ ሥርዓት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 ስር ተዘርግቷል፡፡በዚህ አግባብ ዳግም ዳኝነት እንዲታይ ፍርድ የተሰጠበት ጉዳይ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል የመጨረሻ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ሆኖ ውሳኔው ወይም ትዕዛዙ የተሰጠው በሃሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሰነድን፣ ሃሰተኛ የምስክርነት ቃልን፣ ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቅስ የሆነ ተግባርን መሰረት አድርጎ የተሰጠ መሆኑን አቤት ባዩ ሲረዳው ጉዳዩ በይግባኝ ከመታየቱ በፊት ወይም የመጨረሻ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላም ቢሆን ውሳኔውን የሰጠው ፍ/ቤት ራሱ ዳኝነቱን በድጋሚ እንዲያይ ጥያቄ ለማቅረብ መብት የሚሰጠው ነው፡፡የዚህ ድንጋጌ አላማ በማጭበርበር ወይም በወንጀል ጠቀስ ተግባር የተገኘ ወይም የታጣ መብት ጸንቶ እንዳይቀር ወይም ማንም ሰዉ የወንጀል ድርጊት ተጠቃሚ መሆን የለበትም የሚለዉን መርህ ለማስከበር እንደሆነ እሙን ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርዮአረጸጸምዓለማእየገለግልም!

ዳግም ዳኝነት ይታይልኝ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ከመግባቱ በፊት ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ ይገባዋል ወይም አይገባውም በሚለው ነጥብ ላይ አስቀድሞ ውሳኔ መስጠት የሚገባው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6/4 አነጋገር መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚህ መሰረት ዳኝነት እንደገና ሊታይ ይገባዋል ወይም አይገባዉም ሲል ተገኘ የተባለዉን ማስረጃ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6(1 እና 2) መመዘኛዎች አንጻር መርምሮ ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ ይገባል ወይም አይገባም በሚል በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ እንደማይቻል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6/4 ስር ተደንግጓል፡፡በዚህ አግባብ የተሰጠ ዉሳኔ ይግባኝ ሊባልበት የማይችል እንደመሆኑ እንደመጨረሻ ዉሳኔ ተቆጥሮ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ከሆነ ለሚመለከተዉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ቀርቦ ሊታይ ይችላል፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(1/ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/1 መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ተቀብሎ መመርመር የሚችለዉ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 በአዋጁ አንቀጽ 2/5 ስር በተሰጠዉ ትርጓሜ መሰረት *የመጨረሻ ዉሳኔ ሆኖ በአዋጁ* አንቀጽ 2/4 ስር መሰረታዊ የሕግ ስህተቶች ናቸዉ በሚል የተደነገገዉን አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆነ መመዘኛ የሚያሟላ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ብቻ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ድንበር ታልፏል የተያዘ ይዞታ ለማስለቀቅ ተብሎ ሁከት እንዲወገድ በሚል የቀረበ ክስ የሚመለከት ሆኖ ፍርድ ቤቱ ለዉሳኔ መሰረት ያደረገዉ የተጠሪ ይዞታ ማረጋጫ ካርታ እና የክፍሉ ባለሙያ ባቀረበዉ መግለጫ መሰረት አመልካቾች ወደ ተጠሪ ይዞታ ገብተዉ በመያዝ አመልካቾች የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድ ተብሎ የተወሰነ ስለመሆኑና አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ አስተዳደር አካል እንደገና አጣርቶ ቀድሞ የተሰጠዉ ማስረጃ ስህተት መሆኑን ገልጿል በሚል ዉሳኔዉ እንደገና እንዲታይ አቤቱታ ማቅረባቸዉን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ የማስረጃዉን ይዘት መርምሮ ማስረጃዉ ስህተት ነዉ ያለበትን ምክንያት አያሣይም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን ብይኑ ያሳያል፡፡የማስረጃዉን አግባብነት እና ይዘት በመመርመር አከራካሪዉን ፍሬነገር የማስረዳት ብቃትና አሳማኝነቱን መመዘን ስልጣንና ሃላፊነት የስር ፍርድ ቤት እንጂ የሰበር ችሎት አይደለም፡፡ስለሆነም በማስረጃ ይዘት በመመርመር ስር ፍርድ ቤት የደረሰበትን ድምዳሜ ሰበር ችሎቱ ሊያርም የሚችለዉ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት መኖሩ ሲረጋገጥ ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ ዳግም ዳኝነት እንዲታይ ህጉ የፈቀደዉ በዉስን ምክንያቶች እንደመሆኑ እና ልዩ ሁኔታ እንደመሆኑ ድንጋጌዉ በጠባቡ ሊተረጎም እንደሚገባ ሰበር ችሎቱ በተለያዩ መዝገቦች የሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ ያሣያል፡፡የፍ/ብ/ስ/ስ/ ህግ አንቀጽ 6 አተገባበር አስመልክቶ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ/ 43821ቅጽ8፣ 42871 ቅጽ9 በመ/ቁ/ 93137 እና ሌሎችም መዝገቦች ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ ይመለከታል፡፡ይሁንና አቤቱታዉ ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ የተጠቀሰዉ ሰበር መ/ቁ/91968 ሲሆን በተጠቃሹ መዝገብ ለዉሳኔ መሰረት የሆነዉ አስተዳደር አካል የጻፈዉ ደብዳቤ በሌላ ጊዜ ስህተት ነዉ ተብሎ በመገለጹ ዉሳኔዉ እንደገና ሊታይ ይችላል የሚለዉ ነዉ፡፡በይዘቱም ሲታይ ተከራካሪዎቹ በጋራ ሲጠቀሙ የነበረዉ መጸዳጃ ቤት የአንደኛዉ ተከራካሪ ወገን ብቻ

እንደሆነ ተደርጎ መገለጹን ተከትሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ ለማሳረም የቀረበዉ አዲሱ ማስረጃ መጸዳጃ ቤቱ የጋራ መሆኑን ስለሚያሣይ እንደሆነ ፍርዱ ያመለክታል፡፡በመሰረቱ ሰበር ችሎቱ መ/ቁ/91968 የተሰጠዉ ዉሳኔ ገዥ የህግ ትርጉም ነዉ ወይስ ከቀረበዉ ክርክር አኳያ ማስረጃዉ ሊታይ ይገባል በሚል የተሰጠ ዉሳኔ ነዉ የሚለዉም በራሱ አከራካሪ ነዉ፡፡በተጠቀሰዉ መዝገብ ላይ ክርክሩ ሁከት በሚል የቀረበ ቢሆንም የጋራ መጠቀሚያ የነበረዉን መጸዳጃ ቤት የአንደኛዉ ተከራካሪ ወገን የግል ነዉ ተብሎ የተሰጠዉ ማስረጃ የሌላኛዉን ወገን መብት የሚያሳጣ ከመሆኑ አኳያ ዉሳኔዉ እንደገና እንዲታይ እድል መስጠቱን ያሣያል፡፡

ከዚህ አኳያ የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ክርክር የተነሳበት ይዞታ ወሰን ታልፎ የተያዘ ቦታ መኖር አለመኖሩን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ለዉሳኔ መሰረት ያደረገዉ አስተዳደር አካል የሰጠዉ መግልጫ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል ለተጠሪ የተሰጠ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ጭምር ስለመሆኑ ዉሳኔዉ ያሣያል፡፡አመልካቾች የምከራከሩት ለተጠሪ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሲሰጥ ከአመልካቾች ይዞታ ጋር መደራረብ (overlap) ተፈጥሯል የሚል መግለጫ ቀርቧል በማለት ነዉ፡፡ይሁንና ከፍርዱ በኂላ ቢሆን የአመልካቾች እና የተጠሪ ይዞታ መጠን ተጣርቶና ተለይቶ ያለአግባብ ለተጠሪ የተሰጠ ይዞታ ማረጋገጫ መኖሩ ተረጋግጦ ቀደም ሲል ለተጠሪ የተሰጠዉ ካርታ ስለመምከኑ ወይም ስለመስተካከሉ እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ ለአመልካቾች ይዞታ ማረጋገጫ ስለመሰጠቱ የቀረበ ማስረጃ መኖሩን መዝገቡ አያሣይም፡፡የተጠሪ ካርታ ሲሰራ ከአመልካቾች ይዞታ ጋር መደራረብ ተፈጥሯል ወይሥ አልተፈጠረም፤ መደራረብ ተፈጥሯል ቢባል እንዴት ይታረማል የሚሉ ጉዳዮች ይዞታዉ ይገባኛል የሚሉ ወገኖች ባሉበት በሚመለከተዉ አስተዳደር አካል ተጣርቶ የሚወሰን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ባልተጣራበት ሁኔታ የይዞታ መጠን ልዩነት አለ በሚል ምክንያት የቀደመዉ ፍርድ በሀሰተኛ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ የተወሰነ ነዉ ሊባል አይችልም፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ለተጠሪ የተሰጠዉ ይዞታ ማረጋገጫ ጸንቶ ባለበት ሁኔታ የቀድሞ ልኬት መጠን ስህተት ነዉ የሚል መግልጫ በመቅረቡ ብቻ በሀሰተኛ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ የተሰጠ ዉሳኔ ነዉ በሚል የቀረበዉን አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 6 ድንጋጌ አላሟልም ማለቱ የማስረጃ ምዘና ስህተት አለዉ የሚያሰኝ ምክንያት አላገኘንም፡፡ስለዚህም ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ 91986 ላይ ለዉሳኔ መሰረት ያደረገዉ ማስረጃ እና በዚህ መዝገብ ላይ ለዉሳኔ መሰረት የሆነዉ ማስረጃ በተለይም የተጠሪ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ባለበት ሁኔታ ጉዳዩ ተመሳሳይ ነዉ ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘንም፡፡በሌላ በኩል ቀደም ሲል ክርክር የተደረገዉ ሁከት አለ ወይሥ የለም የሚል እንጂ ይዞታ መፋለም ባለመሆኑ ፍርዱ የባለይዞታነት መብት ለማስከበር የሚቀርብ የመፋለም ጥያቄን የሚያስቀር ጉዳይ አለመሆኑም ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

ሲጠቃለል ቀደም ሲል ሁከት እንዲወገድ ተብሎ የተወሰነዉ የተጠሪ ይዞታ መጠን በይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እና በመሬት ላይ ያለዉ ልኬት መሰረት ተደርጎ መሆኑን እና ይህን ዉሳኔ ለማስለወጥ አመልካቾች ያቀረቡት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርዮአረጸጸምዓለማአ የገለግልም!

አቤቱታ የልኬት ስህተት መኖሩን የሚያሣይ ማስረጃ ተገኝቷል የሚል ሆኖ የስር ፍርድ ቤት ማስረጃዉን መርመሮ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 6 መስፈርት አላሟላም በሚል የሰጠዉ ብይን በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ2(4)) እና 10 መሰረት በዚህ ሰበር ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚያሰኝ ምክንያት የለም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ዉሳኔ**

1ኛ/የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 174750 ላይ በቀን29/10/2015ዓ.ም የሰጠዉ ብይን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1/ሀ/ መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ችሎት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮአረጳጳምዓለማአ የገለግልም!